# ንገሩኝ መቼ እንናደድ

(ግጥም ከሄኖክ የሽጥላ)

የሰከነ የፍቅር ትንፋሽ በደሜ ውስጥ ሰላደረ
ያንቺን የበረከት ቃል ልቤ ፍቅርሽን ኖረ::

እንደ-ቀንድ አውጣ ሳልቡዋችር
ሳልጠቀለል በሆዴ...
የጫት እንጨት ሳልታጠቅ....ሳይሆነኝ ኮባ ጎራዴ....
ማተቤን በጥሼ ሳልጥል
ሳይሆነኝ.....ክፋት ዘመዴ
ትናንትሽን ካድማስ ምዶ
ጠፈር ገምሼ ሳማትር....
ስምሽ በክፉ ሲነሳ....ፊቴ ግንባሬ ሲቆዋጠር....
የድል ዘመንሽ ሃቅ ሆኖ ከፊቴ እየቀደመ
የሚሉኝ ሰምቶ ሳይሆን
አንቺ በሆንሽው ታከመ::

ዛሬም ርቄ በሰው ሃገር ብረት ላይ ከተሰቀለው
ገመድ ካንጠለጠለው
ከፍ ብሎ ያንቺን ሰንደቅ...
ሰማይ ላይ ተፅፎ አየሁ....::
አይታጠፍ ቁመት ሆኖት መቀነት ሆኖት ላድማሱ
ወገቡም የተነቀሰው
ተናግሩዋል ሰማይ  'ራሱ::

አለም...
ግማሽ ነባራዊ ሃቅ....የምር መድረክ ሆኖ
ገጸ-ብህሪይ በፈርጁ...በየመስኩ አሰልጥኖ
ት-ወና-ውን እንዲጫወት አንዱን ቀማኛ  ሲያደርገው...
ሊያውም ከራሱ ማጀት: ከራሱ ኪስ የሚሰርቀው.....
ሰው እንዴት ሽሉን ሲበላ....አንድ ግዜ እንኩዋ አያነቀው?....

ጊዜው ሲያልፍ ማንነቱም...ምንነቱም አብሮ ሊጠልቅ...
ዛሬ መድረኩ የሱ ነው...ተዉት እንዳሻው ያውራ....
...ድንቁርናውን ይራቀቅ::

እናም ዛሬ እንደምታውቂው...
መሬቱን ብቻ አይደለም
ህዝብሽ ምሬቱን ተነጥቁዋል...
ውንድነቱም እንደ "ቅልም ልብስ"
ለሆዱ ሲያድር ለቅቁዋል::

እናም የሆነው ቢጨንቀኝ....
የንደምን ሆነ ይህ ነገር.....የጥያቄ ቃል አነቀኝ::
ይህንን ነደፍኩኝ ላንተ.....
በል ልበልሃ ወገኔ....
አውጫጭኙን ጭኜ መጣሁ...."እንደምን ገዛከ ወያኔ?"

ሃገርህ እንዲህ ትላላች....
ይህንን ጥያቄ ስማኝ....
እንዴት ያንተ ውንድነት እኔን እናትከን ይጥማኝ?

እንግዲህ ዝምታ በልጦ
እንደምስጥ ካ'ፈሩ ስር
ከጨለማ ውስጥ ተቀብረን....
ወይ ሙተን አልበሰበስን
ወይ ቁመን አልተነፈስን....
ውይ ስበን አልተፋሰስን...
መልካ አድር-ባይ ውዳሴ....
"ግንቦት ሃያ" ጎሎጎታን.....
ቀበሌ መቆም  ግብር ሆኖ....በስፍር ስኩዋር ተረታን::

እራሳችንን ፈንግለን...
ተሰብስበን ስንዋረድ....
እስኪ እንግዲህ ንገሩኝ...መቼ በርሃ እንውረድ?
ግራ ገብቶኛል ንገሩኝ እንግዲህ መቼ እንናደድ?....
ወይ እንነጋገር  እንዴ ንዴት ምን እንደሆነ?....
ሰው በቃኝ መቼ እንደሚል....ማ'ስ ጀግና እንደነበረ....
እንነጋገር ንገሩኝ....እምቢኝም ሲቆይ ይረሳል....
ነጻነት "መጣሁ መጣሁ " ሲል
ፍንግል  ነብስ ድሮም ያሳሳል::
ቀን ቁረጡና ንገሩኝ...መቼ ግፉ እንደሚበቃን...
ምን አይነት ንቀት ይሆናል....ካለንበት የሚያነቃን?.....
ቀን ቁረጡና ንገሩኝ....
አውድማው....ባድማ ሆኖ.....
ሀሩር ምድሩን እየመታው....
ረሃብ ወገቡን ታጥቆ....ቀዬ መንደሩን ሲንጠው....
ወንድ እናቱን ከነ ራቡዋ.....ከነስቃዩዋ ጥሎ.....
ሃገር ጥሎ ሲኮበልል....ጎለፈቱን አንጠልጥሎ.....
ተስፋውን ለትንሽ ጅልባ...ለሚንገዳገድ ቀዘፋ
ጸሎቱን ለውሃ ጥፊ....ለውቂያኖስ ላይ ቀፈፋ....
ግብፅ ከነዓን ሆኖ....አድማስ ሲያማትር በተስፋ…
ሃገሩን ለጀርባው ሰጥቶ....ረጅም ውሃ ሲገፋ....
ለዘንድሮው ያገሬ ሰው ....ነጻነት ወይ ክብር ማለት...

ጥልቁን ውሃ እየቀዘፉ...መሞት ነው በውሃ ጭነት
ነጻነት ማለት ህልም ነው....
ነጭ ወረቀት የሚሞሉት
ጅግንነት ሆነ ፍንገላ...እራስን እጣ የሚጥሉት::
ነጻነት መናሳነስ ነው....በገላጭ የሚገኝ ቀመር
ሊቀ-ሊቃውንት አከሌ....ብቻውን ለራሱ ክብር::
ነጻነት ዶክተር መሆን ነው...
ጥበብ የጥበብ አውታር...
ስመ ተክህኖት ደርቦ....ለስደት ሰልፍ መገተር::

ነጻነት....ዝም ማለት ነው....
ዝምታ  ያነቅዛል እንጂ ድሮም....ዝም መቼስ ነቅዞ ያቃል....
እንደማሽላ ነው እሱም.....እያሳረረ ያስቃል::

እና ንገሩኝና.....ተሰብስበን እንናደድ....
ባፍጢማችን ተደፍተን ተዘቅዝቀን ስንዋደድ.....
ንዴትን ጾመን ከሆነም....
ንገሩኝ ምንም አይደለም....
ትንሳኤ የሌለው ፍልሰታ....ድሮም ቢሆን አልነበረም::
እና ንገሩኝ በሞቴ
በየስርጡ ተወሽቀን....
እራሳችን ላይ በሽቀን....
የሚሉንን እየደገምን....ሁነን ከምንሞት በቀቀን....
ምነው ያኔ ስንወለድ....እትብቱ ታጥፎ ባነቀን::

ደሞ ጭንሽን ከፍተሽ.....ለማያውቅሽ አንቺ ታጠኝ....
የሰላም መለከት ነፊ....የቤተ-ሰይጣን ደጅ ጠኝ....::
ላማያውቅሽ አንቺ ታጥኝ...
አንተም ቢሆን ለማያውቅህ..ለልተረዳህ .ጸበል ተረጭ....
በጋኔን ላይ ጋኔን ሲያደር....
ቁልቁል በውሃ ቢገርፉት...
መስቀል አስውጠው ...ቢደግሙት....
ከሰይጣን ሰይጣን ቢወጣም....
የተፈወሰ ሰይጣን ነው....ባንተ ጥሩ ቀን አይመጣም::
ኢትዮጵያዊነት ክብር እንጂ.....
መቼ ሆነና መገበር....
ባንዲራ እያነገቡ: ጀግና እየጠሩ ማጭበርበር......::
እና ንገሩኝ በሞቴ....መቼ ይሆን የሚመቻችሁ....
ለመናደድ እንቃጠር....ባርነት ከሰለቻችሁ....::

አልያ አትደስኩሩ.....

እብቅ ትንፋሽ አታምቁ....ሀሜት ነገር አታክርሩ....
ዝም ብላችሁ ተገዙ.....
ዝም ብላችሁ ዘንድሮም እንድትናንቱ ፈዘዙ.....::
ያደለው ሃገር ይይዛል....
ችዋዴ ግን ክንደ-ብርቱ ነው...
እርጥብ ቅጠሉን አጣምሮ....እግሩን ቆልፎ ይመዛል::.....
መቼ ይሆን ከምር የሚያመን....
መቼ ይሆን ከእባብ እንቅልፍ....
ከጥልቅ አዚም የሚያነቃን.....?
እስኪ ንገሩኝና....ተቃጥረን በቃ እንናደድ.....
ባፍጢማችን ተፈንገለን....በፍቅር ስም ስንዋረድ.....
...በቃ ንገሩኝና....
አንዴ ብቻ እንናደድ...::